M13/1/AXAMH/HP1/AMH/TZ0/XX

22130009

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A: LITERATURE – HIGHER LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A : LITTÉRATURE – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A: LITERATURA – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 1**

Wednesday 8 May 2013 (morning)
Mercredi 8 mai 2013 (matin)
Miércoles 8 de mayo de 2013 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a literary commentary on one passage only.
- The maximum mark for this examination paper is *[20 marks]*.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire littéraire sur un seul des passages.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d’examen est *[20 points]*.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario literario sobre un solo pasaje.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es *[20 puntos]*.


© International Baccalaureate Organization 2013

https://xtremepape.rs/

*ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ ስነጽሁፋዊ አስተያየት ስጥ(ስጭ)፡፡*

**1.**

ከዕለታት አንድ ቀን ፊታውራሪ ኃይሉ በመኖሪያቸው በሚገኘው አዳራሽ ግብር አገቡ፡፡ ከግብር በኋላም ቀረርቶና ፉከራ ሲቀልጥ ዋለ፡፡ ወደ ማታ እኔንና እኒያን ሁለት ወንድማማቾች እየሳሙ፤ «ዛሬ ወደ ዘመዶቻችሁ ትሄዳላችሁ፣ ሌላ ቀን ትመጣላችሁ» ብለው አሰናበቱን፡፡ አብረውን የሚሄዱም ሦስት ሰዎች ተመደቡ፡፡ ፊታውራሪም፤«እሱን ከዘመዶቹ ካደረሳችሁት እነርሱ ወደ አክስቱ ይወስዱታል፡፡ እነርሱን ግን እቤታቸው አድርሱልኝ አደራ» አሏቸው፡፡ ምክንያቱ ምን እንደነበረ ያወቅነው ነገር አልነበረም፡፡ ጉዞውንም ደንገዝገዝ ሲል ጀመርን፡፡

የአባቴን ጠመንጃና ሽጉጥ ትቼ በመመለሴ ግን እንባ ይተናነቀኝ ጀመር፡፡ ጮኬ ለማልቀስም ቃጥቶኝ ነበር፡፡ ከዚያች ጠመንጃ ጋር ልዩ ትዝታ ነበረኝ፤ ተኩስ የጀመርኩት በእርሷ ነበርና፤ ፈሪ እንዳልሆንበት ቄስ ት/ቤት እንዳልገባ ሲከላከል የነበረው አባቴ የእርሱን ወኔና ቆራጥነት ወርሼ ጋሻውን አንስቼ እንደገና የሚመጣውን ጣሊያን በጦር ሜዳና በአርበኝነት እንዳሾቅለት ፅኑ ምኞቱ ኑሮ የበሬ አጥንትና የግንድ ጉማጅ እያስተከለ ተኩሼ እንድመታ ነጋሽ የተባለው ዘመዳችን ኢላማ እንዲያስተምረኝ አዞ ነበር፡፡ ደጋግሜ እስት ስለነበር ተደጋጋሚ ኩርኩም ቀምሻለሁ፡፡ ታዲያ በዚያች ዕለት እሷን ትቼ ስመለስ የአባቴ መሞት አንጀቴን አላወሰው፤ አዕምሮዬን በጠበጠው፡፡ አብረውኝ የነበሩት ጓደኞቼና አጃቢዎቻችን ሲነጋገሩም ሆነ ሲያነጋግሩኝ መነጋገሩ አስጠልቶኝ ነበር፡፡ ፊታውራሪ ኃይሉ በአባትነት ተቀብለው ትምህርት ቤት ቢያስገቡኝም ከአባቴም የበለጡ አለኝታዬ መሆናቸውን ተማምኜባቸው ነበር፡፡ በዚያች ዕለት ግን የአባቴን ጠመንጃና ሽጉጥ ከኔ ነጥለው ሲያስቀሩብኝ የአባቴ ገዳይ መስለው ታዩኝ፡፡ ከዚያም ዕለት በኋላ ያች ጠመንጃና ያችም ሽጉጥ ወደቤታችን አልተመለሱም ወጥተው የቀሩ ታላቅና ታናሽ ወንድማማቾች ሆኑ፡፡ ጨረቃዋ ስትስለመለም የነበረች ይመስለኛል፡፡ ጨለማውም የተጠናከረ ነበር፡፡ መሪ ከሚባለው ወንዝ ከመድረሳችን በፊት ከባድ ተኩስ ሰማን፡፡

«በቃ እርቁ አልሆነም ጦርነት ገጠሙ ማለት ነው፡፡ የኔ ጌታ ጀግናው ኃይሉ ክብረት ይለሽልሸዋል» ብሎ አንደኛው አጃቢያችን ሲደነፋ ከእነዚያ ወንድማማቾች አንዱ፤

«ከማን ጋር ነው ጦርነት የገጠሙት?» ብሎ ጠየቀ፡፡ በዕድሜውም ከሁለታችን ይበልጥ ነበር፡፡

«ከጠላቶቻቸው ጋር ነዋ!» ብሎ ደንፊው መለሰለት፡፡ ፍርሐት እየነዳን መሪ ወንዝ ስንደርስ እየተ ሸከሙ አሻገሩን፡፡ ውሀውም የሚያሰጋ እንዳልነበረ አንዱ ገብቶ ሞክሮት ነበር፡፡ ያ-ወንዝ በድንገተኛ ደራሽ ወስዶን ቢሆን ኑሮ በኔ ቤተሰብ ዘንድ ከፍተኛ ቂም-በቀል በተመሠረተ ነበር፡፡ ምክንያቱም ከብዙ ዓመታት በፊት ላስታ ውስጥ ቡግና ወረዳ ላይ ድባ በሚባለው መንደር ይኖሩ የነበሩት ደጃ ዝማች ብጡል ዘለለው ሞተው የአባቴ እናት ወ/ሮ በየነች ሲነገራቸው፤

«እንግዲህ ወንድሜ ሞቶ ለምን እኖራለሁ? እንዴትስ ወንድሜን ቆሜ እቀብረዋለሁ?» ብለው ከቤ ተሰብ አምልጠው በክረምት ጉርፍ ከአፍ እስከገደፉ ሞልቶ ሲደነፋ ከነበረው መሪ ወንዝ ዘለው ገብ ተው ቀርተዋል፡፡ ይህንኑም ታሪክ በኔ ዕድሜ የሚገኙት ብቻ ሳይሆኑ ተከታዮቻችን ቤተዘመዶች ያውቁታል፡፡



https://xtremepape.rs/

ከረፋዱ ላይ ጥላላ አዚላ ሚካኤል ስንደርስ ዘመዶቼ እየተላቀሱ ተቀበሉኝ፤ አብረውኝ የነበሩትም ወንድማማቾቹን ለማድረስ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ጥላላ ብዙ ቤተዘመዶችና የክርስትና አባቴም ስለነበሩ «ከኔ ጋር ይሁን እኔ ልውሰደው» ሲባባሉ ነበር። ከቀናት በኋላ ግን አክስቴ ሰዎች ልካ ወደ ዓምደወርቅ አስወሰደችኝ። እኔን ካገኘች በኋላም የአባቴ ጠመንጃና ሽጉጥ በመቅረታቸው፤ «ወንድሜ ገና ዛሬ ሞተ፤ ሴት በመሆኔ ተነጠቅሁ። ወንድ ብሆን ኖሮ አይሞክሩትም ነበር» ብላ ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ እኔም ጮኬ አለቀስኩ። ፊታውራሪ ኃይሉ ከነማን ጋር በምን ምክንያት ጦር ነት እንደገጠሙ፣ በጦርነቱም ማን እንዳሸነፈ እሳቸውም እንደሸፈቱ ሰማሁ። እንዲያውም አክስቴ ፊታውራሪ ኃይሉ የገደሏቸው ዘመዶቻችን ስለነበሩ ኃዘን ተቀምጣ ሰንብታለች። በዚያ ወቅት ደግሞ ሴት አያቴና እናቴ ተከታትለው ስለሞቱ፣ የቀረችኝ አለኝታና ተስፋ አክስቴ ብቻ ሆነች። እርሷም ሆነች ሌሎቹ ዘመዶቼ የሙት ልጅነቴ እንዳይሰማኝ ከልብ ይጠነቀቁልኝ ነበር። ዐይና ኢየሱስ የጀመርኩትንም ትምህርት እንድቀጥል የዓምደወርቅ ቂርቆስ መምህር ከነበሩት ከአለቃ ትኩ ዘንድ ስላስገባችኝ ስመኘው ወደነበረው የቤተክርስቲያን አገልጋይነት እንደምሸጋገር ባለሙሉ ተስፋ ሆንኩ።

ማሞ ውድነህ፣ *ማሞ ውድነህ ግለታሪክና ትዝታዎች*፣(2005)።



https://xtremepape.rs/

**2.**

ጸሀይ ወጥታ በጠለቀች፣
በኡደትዋ በቀጠለች፣
ቀዝቃዛውን ባቃጠለች፤

ጨለማውም ኮሶ ፊቱን፣
ሲከሰክስ መታየቱን፤
የከዋክብት ስስ ፈገግታ፣
የጨረቃ ቀዝቃዛ ሳቅ የፌዝ አይነት ውብ ጨዋታ፤
የወፎች ዚቅ ውብ ሙዚቃ፣
ጎህ ሲፈካ በተንቃቃ፣ በተብቃቃ፣
በነፋሳት የጣር ሲቃ፣
ምድር ስትሾር ስትንቃቃ፣
«አለም ማለት ይችው በቃ»፣
ሲል ከዋለ ካልዋለለ፣
ካልፈጠረ፣ ካልታገለ፣ ለዚህ ደሞ ካልታደለ፣
የለም እኮ! ምኑን አለ?

የምድር ተኩላ ያየር ሲላ፣
ያገኘውን እየበላ፣ ቀርበታውን እየሞላ፣
እንደሚሉት «እዚያው ሞላ፣ እዚያው ፈላ»፣
ቢኖር እንኳዋ በጅል መላ፣
«የለም» በሉት ባለም ገላ።
ለወገኑ ሻማ ሆኖ ካልነደደ፣
እሱን ብቻ ከወደደ፣
ለከርሱ ሲል ያገሩን ክብር ካዋረደ፣
ጥንቱኑ ነው ወደቀብሩ የነጎደ።

«ለምን?» ብሎ ካልጠየቀ፣
እመቀ ምድር ካልጠለቀ፣
ከሰማያት ካልመጠቀ፣
እንዳሳማ ከርሱን ብቻ ከጠበቀ፣
ታሪክ ሰርቶ ካልደመቀ፤
ቢተነፍስ፣ ቢንቀሳቀስ ያለ መስሎ፣
ሙትቻ ነው የሰው ቆሎ።

ካላረሰ ካልፈለሰ፣
የምድሩን ሆድ ካላሰሰ፣
የእጁን ጣቶች እየላሰ ለቁርጥ ለት ካልደረሰ፤
አልቅሱለት ድሮ ሞቶዋል፣
የእንግዴ ልጅ ሆኖ ቀርቶዋል።



https://xtremepape.rs/

እንዳሞራ ካልበረረ፣ እንደጅግራ ካልሰገረ፣
ቢሞት እንኳዋ ካልተጠራ፣ ግብረ ስሙን ካልዘከረ
ከተረሳ፣ ካልተወሳ፣ በዚች አለም እንደኖረ፣
«አለሁ» ቢልም አልነበረ።

ለሃቅ ሲል ባደባባይ ካልሞገተ፣
በበረሃ ካልዋተተ፣ ባድባር ዋይታ ካልባተተ፣
ካልዘመተ፣ ካልከተተ፣
እሱን ብቻ ሲያሽሞነሙን እሱ በእሱው ከሻገተ፣
እባካችሁ ደረት ድቁ ሲወለድ ነው የሞተ።

አበረ አዳሙ፣ *ውዳሴ ሞት*፣(2009)።



https://xtremepape.rs/